የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 32
ADDIS ABABA, 23rd February, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፭/፪ሺ፯ ዓ.ም

ለአህጉራዊ የዘላቂ አርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ…………ገጽ ፰ሺ፩፻፵፫

CONTENTS

Proclamation No. 885/2015

International Development Association Financing Agreement for Financing the Regional Pastoral Livelihood Resilience project, Ratification Proclamation…..Page 8143

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፭/፪ሺ፯

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአህጉራዊ የዘላቂ አርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፵፱ ሚሊዮን ፬፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኝ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ህዳር ፲፱ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No. 885/2015

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount equivalent to forty-nine million four hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 49,400,000) for financing the Regional Pastoral Livelihood Resilience Project, was signed in Addis Ababa on the 28th day of November, 2014;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 29th day of January, 2015;

NOW,THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.60

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለአህጉራዊ የዘላቂ አርብቶ አደር ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፭/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ህዳር ፲፱ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው ብድር ቁጥር 5545-ET ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፵፱ ሚሊዮን ፬፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for financing the Regional Pastoral Livelihood Resilience project, Ratification Proclamation No.885/2015".

**2. Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Credit number 5545-ET signed on the 28th day of November, 2014 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of equivalent to forty-nine million four hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 49,4000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing agreement.

**4. Effective Date**

This proclamation shall come into force on the Date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 23st day of February, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**